DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

**ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች: ስለ ተርም (Term) 4 ደረጃ አሰጣጥ፣ ወደ ሌላ ክፍል ማደግ እና ምርቃት**
***አዲስ ወይም ማሻሻያዎች – ሚያዝያ (April) 2020***

በክልላችን በኮሮናቫይረስ COVID-19 ስርጭት ምክንያት፣ በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) የቤት ውስጥ መማር፣ አሁንም፤ በዚህ የትምህርት ዓመት ማብቂያ እስከሚሆንበት፣ እስከ አርብ፣ ግንቦት 21 (May 29) ድረስ ይቀጥላል። ይህ የቀን መቁጠሪያ (calendar) ሽግሽግ መደረግ፤ ተጨማሪ፣ የታቀደ የበጋ (summer) ትምህርት አማራጮች እንዲኖሩ ለማድረግ፣ እንዲሁም የጤና ሁኔታዎች የበለጠ ተስማሚ በሚሆንበት ጊዜ፣ የ2020-2021 የትምህርት ዓመትን ለመጀመር፤ ጊዜውን ለመጠበቅ ዕድል ይሠጠናል።

በዚህ በአሁኑ የትምህርት ዓመት የቀን መቁጠሪያ (calendar) ለውጦች ሳቢያ፣ DCPS የተርም (term) 4 ደረጃ አሰጣጥን ፖሊሲዎችን፣ የተማሪዎች ወደሌላ ክፍል ማደግን ግልጽነት በተሞላበት ሁኔታ መስጠት፣ እና ለ2020 ተመራቂዎች (class of 2020) በምርቃት መስፈርቶች ላይ መመሪያን መስጠት ላይ  አዲስ ወይም ማሻሻያዎችን ይሠጣል። DCPS በዚህ ታይቶ የማይታወቅና አስቸጋሪ ጊዜ፣  በስርዓተ ትምርህታቸው በቤት ውስጥ መማር እና ተለዋዋጭ የደረጃ አሰጣጥ፣ ወደ ሌላ ክፍል ማደግ፣ እና የምርቃት ፖሊሲዎች ላይ እርዳታን ለተማሪዎች ለመስጠት በትጋት ይሠራል።

ቤተሰቦች በእነዚህ ርዕሶች ላይ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሏቸው፣ እባክዎን ለትምህርት ቤትዎ ጥሪዎን ያቅርቡ።

- ገጽ (Page) 1 – ተርም (Term) 4 ደረጃ አሰጣጥ
- ገጽ (Page) 4 – ወደ ሚቀጥለው ክፍል ማለፍ
- ገጽ (Page) 5 –  የ2020 (Class of 2020) ምርቃት

## ተርም (TERM) 4 ደረጃ አሰጣጥ

### ጥ1. ለተርም (term) 4 የተያዘው የጊዜ አቀማመጥ ምንድነው?

ተርም 4 ከሰኞ፣ ሚያዝያ 19 (April 27) ይጀምር እና እስከ አርብ ግንቦት 21 (May 29) ድረስ ይቆያል። ምናባዊ (virtual) የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባ ቀን፣ ግንቦት 14 (May 22) ይደረጋል። እንዲሁም ሰኞ ግንቦት 17 (May 25) ቀን፣ የ'Memorial Day' በዓል ስለሆነ በቤት ውስጥ መማር አይኖርም፤ DCPSም ለሁሉም አስተማሪዎች እና ሠራተኞች ዝግ ይሆናል።

### ጥ2. በተርም (term 4)፣ የቤት ውስጥ መማር የክንውን ሂደት ላይ የተደረገ ማንኛውም ለውጦች ይኖራሉን?

የለም። እያንዳንዱ ተማሪ በዚህ በቤት ውስጥ መማሪያ ወቅት፣ የታተሙ የመማሪያ ጥራዞችን በማግኘት ወይም የኦንላይን ዕድሎችን በመጠቀም፣ በትምህርቶቻቸው በመሳተፍ እንደሚቀጥሉ እንገምታለን። ሣምንት 6 እና 7ን የሚሸፍነው የታተመ ጥራዝ፣ በሚያዝያ 19 (April 27) ሣምንት ዝግጁ የሚሆኑ እና እንደገና በግንቦት (May) ወር ውስጥ ደግሞ፣ ከ8 እስከ 10 ሣምንታት ውስጥ የሚካሄዱትም ለስርጭት ዝግጁ ይሆናሉ፤ የሁሉም ተማሪዎች መማሪያዎች ከካንቫስ (Canvas) በbit.ly/DCPS_ICP በማውረድ (download) ይገኛሉ።

ተማሪዎች፣ ከቀለም ትምህርቱ ላይ አዲስ ቁሳቁሶችን በሣምንታዊ እንቅስቃሴዎቹ ውስጥ በማካተት፣ በቀጥታ ከአስተማሪዎቻቸው ጋር በመሆን መሳተፋቸውን መቀጠል አለባቸው። ሆኖም፣ በርካታ ፈታኝ የሆኑ ነገሮች ተማሪዎችን እንደሚገጥማቸው በማወቅ፣ በቤት ውስጥ መማር ሂደቱ ላይ አንዳንድ ጊዜያትን ለመካፈል ያለመቻል ሁኔታ እንደሚገጥምዎ እንገነዘባለን። ለዚህም አስተማሪዎች ምላሽ በመስጠት፣ ተማሪዎች በመማር ሂደቱ በሌላ ጊዜ (asynchronously) የሚደረግበትን መንገድ (የተቀዱ ትምህርቶችን በእርስዎ አመቺ ጊዜ እንዲያገኙ በማድረግ)፤ እንዲጠቀሙ በመፍቀድም እንጂ፣ በቀጥታ ምናባዊ ትምህርቱን (live virtual lesson) ከክፍላቸው ጋር ብቻ አያካሂድም።

የቤተሰብዎን ተመራጭ ከሆኑ መንገዶች ጋር በሚያስማማ ሁኔታ፣ መማሩ እንዲቀጥል እንፈልጋለን፤ እንዲሁም በCOVID-19 ምክንያት በተወሰደ አስቸኳይ እርምጃ ትምህርት ቤቶችን በመዘጋታችን ሳቢያ የተማሪው የቀለም ትምህርት ሁኔታ፣ ከፉኛ የሆነን ተፅዕኖ እንዳያስከትል እንፈልጋለን።

**ጥ3. በተርም (term) 4 ከቤት ውስጥ ሆኖ መማር ሂደት ላይ የተማሪዎች ስራዎችን እንዴት ነው ደረጃ የሚሰጣቸው?**

በተርም (term) 4፤ ለመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች (K-5) እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች (6-12) ደረጃ አሰጣጦች እንደሚከተለው ይሆናል።

<u>የተርም (Term) 4 የመጀመሪያ ደረጃ፣ የደረጃ አሰጣጥ</u>

በተርም (Term 4)፣ በይዘት ስፍራው በተደጋጋሚ በመካፈል (ቢያንስ በሣምንት 2 ጊዜ) በቤት ውስጥ መማር የቤት ሥራዎች (assignments) እና እንቅስቃሴዎች የተካፈሉ ተማሪዎች፣ “P” (ማለፊያ/pass) ያገኛሉ። በይዘት ስፍራዎቹ ውስጥ ለመካፈልና በቤት ውስጥ መማር የቤት ሥራዎችን (assignments) እና እንቅስቃሴዎች ላይ መካፈል ያልቻሉ ተማሪዎች፣ “NM” (ማርክ የሌለው/no mark) በሚል ይመደባሉ።

<u>የተርም (Term) 4 ሁለተኛ ደረጃ፣ የደረጃ አሰጣጥ</u>

በዚህ ጊዜ ውስጥ አስተማሪዎ የፈተና አሰጣጥን ለመቆጣጠር በማይችሉበት ጊዜ፣ ተማሪዎች በቤት ውስጥ መማር ሂደቱ ላይ አቅማቸው በሚፈቅድ መጠን ጥረት በማድረግ እንደሚሳተፉ ግምታችን ነው። ለሁሉም ከ6ተኛ እስከ 12ተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን በቀለም ትምርህት ውጤታቸው መሻሻል እንዲያመጡ እድል ለመስጠት፣ የተርም (term) 4 የደረጃ አሰጣጦች፣ በልምምድና መተግበር እና ተሳትሮ መካከል ዕኩል በሆነ ሚዛን የሚፈጥር ደረጃዎች በመስጠት ሲሆን፣ ተጨማሪ ክሬዲት (extra credit) ለማግኘት የሚያስችል ሣምንታዊ ዕድሎች አሉ፤ እንዲሁም እነዚህ ስራዎችን ካለምንም ቅጣት፣ በማንኛውም ጊዜ ጨርሶ ማስገባት ይቻላል። ተማሪዎች የተርም (term) 4 ደረጃዎችን ከ“A እስከ F” በሆነ መለኪያ ይሰጣቸዋል።

<table>
<tr><th>ልምምድ እና  መተግበር (Practice & Application)</th><th>ተሳትፎ (Participation)</th></tr>
<tr><td>የውጤቱ 50% የሚሸፍነው ሁሉንም የጥራዝ ስራዎች መሸፈን እና ሌሎች የቤት ስራዎችን (assignments) ማጠናቀቅ።</td><td>የውጤቱ 50% ጥቅም ላይ የሚውለው፣ በቤት ውስጥ መማሩ ላይ በመካፈል ነው። ይህም ሊያካትት የሚችለው፤ በ’real time’ ትምህርቱን መመልከት እና ከአስተማሪዎች ጋር ተሳትፎ ማድረግ፣ ወይም ተማሪው በኋላ፤ በራሱ የጊዜ ሰሌዳ አሰራር መሠረት፣ የሐሳብ ትንተና በማከናወንም ሊሆን ይችላል።</td></tr>
<tr><td colspan="2">በተርም (term) 4፣ አስተማሪዎች በሣምንት ሁለት የቤት ሥራዎችን (assignments)፣ እያንዳንዳቸው አንድ ዓይነት የነጥብ ቁጥር ያላቸው ሊሰጡ ይችላሉ። አንደኛው የቤት ሥራ (assignment) እንደ መደበኛ ክሬዲት (credit) እና የሚቀጥለው ደግሞ እንደ ተጨማሪ ክሬዴት (extra credit) ሊቆጠር ይችላል።</td></tr>
</table>

**ጥ4. ለ2019-2020 የትምህርት ዓመት፣ የመጨረሻ የደረጃ ውጤቶችን እንዴት ተደርገው ይሠላሉ?**

የዚህ ዓመት የመጨረሻው የደረጃ ውጤት አሰጣጥ የሚሰላው፣ የተማሪዎቹን ፍላጎት በጥሩ ሁኔታ የሚጠብቅ ሆኖ እንዲያገለግል ተደርጎ፣ ለማጠናቀቅ በቻሉት ስራዎቻቸው ላይ ትኩረት በመስጠትና ከዚህ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ክሬዲት (credit) በመስጠት ነው።

<u>የመጀመሪያ ደረጃ (Elementary)</u>

በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች፣ የመጨረሻ የደረጃ አሰጣጦችን አይቀበሉም። ከዚህ በላይ እንደተዘረዘረው የተርም (Term) 4 ደረጃን ያገኛሉ።

<u>የሁለተኛ ደረጃ (Secondary)</u>

*የሙሉ ዓመት ኮርሶች*
የመጨረሻው የውጤት ስሌት የሚሰላው፣ በሁሉም ተርም (term) ውስጥ ያገኟቸው ውጤቶች አማካኝ ውጤት ተወስዶ ነው። የተማሪው የመጨረሻ ውጤት በተርም (term) 4 ውስጥ፣ ከሌሎቹ ተርሞች 1-3 አማካኝ ውጤት የበለጠ ከሆነ፣ ከፍተኛውን የውጤት ደረጃን እንዲያገኙ ይደረጋል። ነገር ግን የተርም (term) 4 ውጤቱ፣ ከሶስቱ-ተርሞች አማካኝ የሚያስ ከሆነ፣ የተርም (term) 4 ውጤት በመጨረሻ ስሌቱ ላይ እንዲዘለል ይደረጋል።

*የሴሚስተር ኮርሶች*
ለሁለተኛው ሴሚስተር ውጤቶች የመጨረሻ ስሌት የሚሆነው፣ የተርም (term) 3 እና ተርም (term) 4 አማካኝ ውጤቶች ናቸው። ሆኖም ግን የተርም (term) 4 ውጤታቸው ከተርም (term) 3 ውጤታቸው ያነሰ ከሆነ፣ የመጨረሻ ውጤት ሆኖ በቀላሉ ሊወሰድ የሚችለው የተርም (term) 3 ውጤት ነው።

*ማስታወሻ: በተርም (term) 4 ውስጥ ተማሪዎች ምንም ዓይነት ስራዎችን ላለማከናወን ቢወስኑ፣ "I" (ያልተጠናቀቀ/incomplete) በሚል ለኮርሱ ሊያገኙ የሚችሉትንና ለመጨረሻው ውጤታችውን ለማመላከት የሌሎች ተርም (ሞች) አማካኝ የሆነ ውጤታቸው ላይ ብቻ ተመርኩዞ፣ ስራቸው ይሰላል።*

**ጥ5. የመጨረሻ ውጤቶች በሪፖርት ካርዶች ላይ እና በትምህርት ውጤት ማስረጃ (ትራንስክሪፕቶች) ላይ እንዴት ይመዘገባሉ?**

ለSY19-20 ለሁሉም የመጨረሻ ውጤቶች፣ በሪፖርት ካርዶች ላይ እና በትምህርት ውጤት ማስረጃ (transcripts) ላይ እንደሚከተለው ይመዘገባሉ:

| *ከ A-F መለኪያ መሠረት የተገኘ ውጤት (Grade)* | *በትምህርት ውጤት ማስረጃ (Transcript) ላይ የሠፈረ ውጤት* | *ምክንያትያዊ ትንታኔ (Rationale)* |
|---|---|---|
| A | A | A ወይም B ያገኙ ተማሪዎች፣ ይህ ውጤታቸው፣ በትምህርት ውጤት ማስረጃ (transcript) እና ተዛማጅ የሆነ የGPA መመዘኛዎቻቸው ላይ በማስፈር ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል። |
| B | B | |
| C | P | C ወይም D ያገኙ ተማሪዎች፣ ይህን ዝቅተኛ ውጤት በማስፈር አይቀጡም። በአንፃሩ ግን፣ "P" (ማለፊያ ውጤት) በሚለው ይመደብና፣ በGPA ላይም ገለልተኛ (neutral) መሆንን ያሳያል። |
| D | P | |
| F | I | በመጨረሻ ውጤታቸው የወደቁ ተማሪዎች፣ "I" ለincomplete/ያልተጠናቀቀ የሚለውን በማመልከት ይመደባሉ። እስከ መስከረም (January 2021) ድረስ በኮርሱ የማለፊያ ውጤትን እንዲያገኙ ጊዜ ይኖራቸዋል። |

የC እና D ፊደልን በውጤታቸው ላይ እንዳለ እንዲሰፍር የሚፈልጉ ተማሪዎች፣ ወይም የA እና B የፊደል ውጤቶቻቸው እንደ "P" ሆነው እንዲሰፍሩ የሚፈልጉ ተማሪዎች፤ ማስተካከያዎቹ በትምህርት ውጤት ማስረጃዎቻቸው (transcript) ላይ እንዲስተካከሉ መጠየቅ ይችላሉ። ተማሪዎቹ የትምህርት ቤት አማካሪውን (counselor) በማነጋገር፣ ማስተካከያው እንዲደረግ መጥየቅ ይችላሉ።

**ጥ6. በተርም (term) 4 ውስጥ፣ የ'Opportunity Academy' ወይም የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ (Credit Recovery) ኮርሶች እንዴት ነው ደረጃ የሚሰጣቸው?**

<u>የ'Opportunity Academy' የደረጃ አሰጣጥ</u>
በመማሪያ መድረኮቻቸው ላይ ያላቸውን ኮርሶች እንዲያጠናቅቁ፣ አስተማሪዎች ከተማሪዎች ጋር መስራታቸውን መቀጠል ይጠበቅባቸዋል። በተለመደው የትምህርት ዓመት ማብቂያ ላይ የተሰጣቸውን ኮርሶቻቸውን ማጠናቀቅ ያልቻሉ ተማሪዎች፣ የ"I"

ውጤቶች እንዲያገኙ የሚያደርጋቸው እና በእነዚህ ኮርሶች እስከ መስከረም (January 2021) መስራታቸውን ቀጥለው እንዲያጠናቅቁ እድል አላቸው። አስተማሪው፣ ከትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ጋር በመተባበር፣ ምናልባት ተማሪዎችን ከመጋቢት 4 (March 13) በኋላ የተሰጧቸውን የኮርስ ስራ ነፃ እንዲሆኑ ሊያደርጉ ይችላሉ። የመጨረሻ ውጤት ይዘቶቻቸውን በትምህርት ውጤት ማስረጃ (transcript) ላይ የሚሰፍርበትን ሁኔታ ከላይ እንደሚታየው ተገልጿል።

<u>የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ (Credit Recovery) የደረጃ አሰጣጥ</u>

የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ (Credit recovery courses) እስከ ተርም (term 4) መጨረሻ ድረስ ሊቀጥል ይችል ይሆናል። እነዚህ ክፍለጊዜዎች፣ ብቃትን መሠረት ያደረገ እና በግል የመጓዣ ፍጥነት የተቀረጸ በመሆኑ ምክንያት፣ በውጤቱ ላይ የሚጠበቀው አንድ ዓይነት በሆነ ሁኔታ የሚቆይና ከላይ ከታየው የማሻሻያ መለኪያ እና ስሌት የተለየ ነው። እንደ ሁልጊዜው፣ ውጤቶች በሚከተሉት ላይ መሠረት ያደረጉ መሆን አለባቸው:

- 50% የተማሪ ልምምድ እና መተግበር (Practice & Application)
- 50% ግምገማ (በክሬዲት መልሶ ማነሳሻ (credit recovery) ኮርሶች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች፣ የቀለም ትምህርት ሐቀኝነት ቃል መግቢያን መፈረም አለባቸው)

የመጨረሻ የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ (credit recovery) ውጤቶች እንደሚከተለው የሚሰፍሩ ሲሆን፣ እና እንደ ሁልጊዜውም፣ የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ (credit recovery) ኮርስ ውጤቶች፣ በተማሪው የትምህርት ውጤት ማስረጃ (transcript) ላይ ያለውን ዋናውን (original) የክሬዲት ኮርስ ውጤቶችን አይተካውም።

| *ከ A-F መለኪያ መሠረት የተገኘ ውጤት (Grade)* | *በትምህርት ውጤት ማስረጃ (Transcript) ላይ የሠፈረ ውጤት* | *ምክንያትያዊ ትንታኔ (Rationale)* |
|---|---|---|
| A | A | A ወይም B ያገኙ ተማሪዎች፣ ይህ ውጤታቸው፣ በትምህርት ውጤት ማስረጃ (transcript) እና ተዛማጅ የሆነ የGPA መመዘኛዎቻቸው ላይ በማስፈር ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል። |
| B | B | |
| C | P | C ወይም D ያገኙ ተማሪዎች፣ ይህን ዝቅተኛ ውጤት በማስፈር አይቀጡም። በአንፃሩ ግን፣ "P" (ማለፊያ ውጤት) በሚለው ይመደብና፣ በGPA ላይም ገለልተኛ (neutral) መሆንን ያሳያል። |
| D | P | |
| የክሬዲት መልሶ ማነሳሻ (credit recovery)፣ ኮርሱን ማጠናቀቅ ያልቻሉ ተማሪዎች፣ "W" (የወጡ/withdrawn) በሚል ይመደባሉ። | | |

### ወደሚቀጥለው ክፍል ማለፍ

**ጥ7. ምን ምክንያቶች ናቸው፣ ተማሪው በK-8 ባሉ ክፍሎች ውስጥ ማለፉን የሚወስነው?**

ግንቦት 7 ቀን (May 15)፣ ትምህርት ቤቶች ወደሚቀጥለው ክፍል ለማለፍ የሚፈለገውን መስፈርት[1] የማያሟሉ ተማሪዎች እነማን እንደሆኑ ለቤተሰቦች በማሳወቅ፣ ለሚቀጥለው ዓመት ለተማሪው ፍላጎት ተመራጭ የሆነውን መንገድ ለመወያየት ያነጋግራል። በዚህ የተራዘመ የትምህርት ቤት መዘጋት ወቅት፣ ማንም ተማሪ በትምህርት ገበታ በአካል ተገኝተው የሚሰጡትን የማስተካከያ እርዳታዎችን ባለማግኘታቸው ምክንያት ወደሚቀጥለው ክፍለ ከማለፍ የሚያግድ ቅጣት አይደርስባቸውም።

ለትምህርት ዓመት 2020-2021፣ ቤተሰቡ እና ትምህርት ቤቱ በጋራ ለተማሪው መድገሙ ተመራጭ የሆነ እንደሆነ ካልተስማሙ በስተቀር፣ ማንም ተማሪ እንዲደግም አይደረግም። በተጨማሪም፣ ምንም እንኳን ቤተሰቡ እና ትምህርት ቤቱ ይህ

---

[1] Per DC Municipal Regulations (5-E DCMR § 2201.6), in order to be promoted to the next level, students in pre-K through 8th grade must receive proficient or advanced marks in core subjects and comply with the system's attendance policy.

መድገም ለተማሪው ተመራጭ የሆነ ነው ብለው ቢያምኑም እንኳን፣ አንድ ጊዜ የደገሙ ተማሪዎችን እንደገና ለሌላ ዓመት እንዲደግሙ አይደረግም።

**ጥ8. ለሚቀጥለው ዓመት ምን ዓይነት የተማሪ እርዳታዎች ይሰጣሉ?**

በተራዘመው የትምህርት ቤት መዘጋት በፈጠረው ክፍተት ሳቢያ፣ የሚቀጥለው ዓመት ብዙ ተማሪዎች ተጨማሪ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው እናውቃለን። የመዛወሪያ መስፈርቶችን ሳያሟሉ ላለፉ ተማሪዎች፤ ለሚቀጥለው ዓመት፣ ጠንካራ የእርዳታ ዕቅድ ለማዘጋጀት ትምህርት ቤቶች ኃላፊነት አለባቸው። ስለእርዳታ ዕቅዶቹ ተጨማሪ መረጃዎች፣ ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች በቀጥታ ከትምህርት ቤቶቻቸው ይደርሷቸዋል። በተጨማሪም፣ የቀለም ትምህርት ክፍተቶች ለታዩባቸው ተማሪዎች እርዳታን በማካተት፣ DCPS ለሚቀጥለው ዓመት ጠንካራ አጀማመር እንዲኖረው የቀለም ትምህርት ዕቅድ ላይ እየሰራ ይገኛል።

**ጥ9. በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከክፍል ወደክፍል ማለፊያ ውጤቶች ላይ የሚደረጉ ማንኛውም ለውጦች ይኖራሉ?**

የለም። ከ9-11 ከክፍል ወደክፍል የማለፊያ ውጤቶች በምርቃት ክሬድት ማጠራቀም (graduation credit accrual) ላይ መሠረት ያደረገ ነው።

## የ2020 (CLASS OF 2020) ምርቃት

**ጥ10. በ2019-2020 የትምህርት ዓመት ለምርቃት የሚያስፈልገው የክሬዲቶች ቁጥር ላይ ለውጥ አለ?**

የለም። ተማሪዎች አሁንም ቢሆን የተለመደውን የDCPS ዲፕሎማ (በፕሮግራም ጥናት ላይ እንደተገለጸው፣ ልዩ (specialty) ዲፕሎማዎችን ለማግኘት ደግሞ ተጨማሪ ክሬዲቶችን) ለመያዝ፣ አጠቃላይ 24 ክሬዲቶችን ማግኘት አለባቸው።

በክሬዲት መልሶ ማነሳሻ (credit recovery) "W" ወይም "I" በመደበኛ ኮርስ ያገኙ ተመራቂ ሊሆኑ የሚችሉትን ሁሉ፣ በዚህ በጋ (summer)፣ የማለፊያ ኮርስ አማራጭ ዝርዝሮች ሲወጡ እንዲያገኙ ለመርዳት፤ ትምህርት ቤቶች በንቃት ክትትል ሊያደርጉባቸው ይገባቸዋል። በበጋው (summer) ወቅት፣ በ0.5 እና 3.0 መካከል ያሉ ክሬዲቶች የቀሯቸው ተመራቂ ሊሆኑ የሚችሉ ተማሪዎች፣ በክሬዲት መልሶ ማነሳሻ (credit recovery) እና የ'twilight' ኮርሶችን ማግኘት አለባቸው።

**ጥ11. በቤት ውስጥ በመማር ወቅት፣ ተማሪዎች የማህበረሰብ አገልግሎት (community service) ሰዓታቸውን ሞልተው ማጠናቀቅ ይጠበቅምባቸዋልን?**

በ2020ው፣ የCOVID-19 ምላሽ አሰጣጥ ተጨማሪ የአስቸኳይ ጊዜ ማስተካከያ ድንጋጌ (COVID-19 Response Supplemental Emergency Amendment Act of 2020) መሠረት፣ የ100-ሰዓት የማህበረሰብ አገልግሎት (community service) መስፈርትነት፣ ለዚህ የትምህርት ዓመት (class of 2020) ተመራቂዎች ብቻ ተነስቷል። ሙሉ የ100-ሰዓት መስፈርት በሚቀጥለው ዓመት እንደገና አገልግሎት ላይ ይውላል ተብሎ ይጠበቃል።

**ጥ12. አሁን፣ ግንቦት 21 (May 29) ትምህርት ቤት የሚያበቃ ስለሆነ፣ መቼ ነው የምርቃት ስነ ስርዓቶች የሚደረጉት?**

DCPS፣ የ2020 ተመራቂዎችን (class of 2020) የክንውን ፍፃሜያቸውን ለማክበር መንገዶችን በመፈለግ ተግቶ ይሠራል። ስለ ምርቃት ስነ ስርዓት አማራጮችን እና ሌሎች የሲኒየር (senior) እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ፣ እነዚህ እንቅስቃሴዎች በዚህ ፀደይ (spring) ወቅት በአካል በመገኘት ለመካሄድ መቻል አለመቻላቸውን፣ በቅርብ ጊዜ የሚወጡ ተጨማሪ መረጃዎች ይኖራሉ።